የወ/መ/ቁጥር 156514

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ ወ/ሮ ኑኑሽት ይልማ በሽር - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ መስከረም 20 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 665(1) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ነሐሴ 06 ቀን 2000 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 7፡00 ሰዓት ሲሆን በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11 ክልል ልዩ ቦታው ተክለሐይማኖት ቤተክርስቲያን አካባቢ የግል ተበዳያ ወ/ሪት ሲቲ ሸሪፍ አንገት ላይ ተበጥሶ የወደቀውን አስራ ሁለት ግራም ባለ ሃያ አንድ ካራት የወርቅ ሀብል ግምቱ ብር 2400.00(ሁለት ሺህ አራት መቶ) የሆነ በመውሰዷ በፈፀመችው የስርቆት ወንጀል ተከሳለች በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሷትና ተነቦላት ከተረዳችው በኋላ ክሱን ሳትቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብላ ክዳ በመከራከሯ ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሦስት ምስክሮችን በማቅረብ ያሰማ ሲሆን የተሰሙት ምስክሮችም በሰጡት ቃል በወቅቱ የግል ተበዳይና ተከሳሽ ተጣልተው የተያያዙ ሲሆን፤ ሰዎች ሲገላግሏቸው ከግል ተበዳይ አንገት ላይ የነበረ የወርቅ ሐብል መሬት ላይ ሲወድቅ ተከሳሽ ይዛው መሄዷን በቦታው የነበሩና ያዩ ምስክሮች በማስረዳታቸው ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 665(1) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ የስርቆት ድርጊቱን መፈፀሟን እንድትከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዛለች።

ተከሳሽም እከላከላለሁ በማለት ሦስት የመከላከያ ምስክሮችን ያቀረበች ሲሆን የሚያስረዱበት ጭብጥም በወቅቱ ንብረቱን ያለመውሰዷን፤ በዕለቱ ከጠዋቱ 5፡00 ሰዓት ሲሆን ጎረቤቴ ወ/ሮ ማሜ ንብረት ጠብቂልኝ አደራ ብላኝ እየከበኩ ነበር፤ የሚመጣ መኪና ነበር፤ ከግል ተበዳይ ጋር አልተያያዝኩም፤ የግል ተበዳይ ነው፤ የሰደበችኝ፤ ይህንም አስረዳለሁ የሚለውን ሲሆን የመከላከያ ምስክሮቹም ቀርበው መኃላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ባቀረበችው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባትን ክስና ማስረጃ አስተባብላለች ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮች በወቅቱ የግል ተበዳይና ተከሳሽ ተጣልተው ተያይዘው ነበር፤ እኛ ነን ያገላገልናቸው በማለት የገለፁ ሲሆን፤ ተከሳሽ ግን ጭብጡን ሲያስመዘግቡ በወቅቱ ከግል ተበዳይ ጋር አልተያያዝንም ብለዋል። ከዚህ ሌላ በወቅቱ የግል ተበዳይ ወርቄን እያለች ስትናገር ነበር በማለትም

ምስክሮቹ አስረድተዋል። ነገር ግን ወርቅ ተከሳሽ ስለመውሰዱ ወይም አለመውሰዱ የምናውቀው ነገር የለም በማለት ገልፀዋል። በዐ/ሕግ በኩል ከቀረቡት ምስክር ውስጥ አንዷ ጎረቤት መሆናቸውን ገልፀው በወቅቱ ተከሳሽ የግል ተበዳይን ወርቅ ከመሬት በማንሳት ስትወስድ በማለት አስረድተዋል። አሁን በተከሳሽ በኩል የቀረቡት ምስክሮች ግን ተከሳሽ የወርቅ መውሰድ ድርጊቱን አልፈፀመችም በማለት ጥርጣሬን በሚፈጥር መልኩ አላስረዱላትም። በመሆኑም ተከሳሽ ባቀረበችው የመከላከያ ምስክር በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል ያልቻለች ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 665(1) ስር ጥፋተኛ ናት በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ በመመሪያው በወጣለት ደረጃ መሰረት የሚያርምና የሚያስተምር ቅጣት

እንዲወሰን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 35 ዓመት ነው፤ ትዳር የለኝም፤ አንድ የ 10 ዓመት ልጅ አለኝ፤

በባለቤቴ ጡረታ ነው የምንተዳደረው፤ የቀን ሥራ እሰራ ነበር፤ ነገር ግን

አረብ አገር ሄጄ ከፎቅ ላይ ወድቄ ወገቤ የተጎዳ በመሆኑ አሁን ተንቀሳቅሼ

ለመስራት አልችልም። ከግል ተበዳይ ጋርም ታርቀን በሰላም እየኖን ነው

ስትል፤ ዐ/ሕግም አዎ የግል ተበዳይና ተከሳሽ የታረቁበት ሰነድ ከእኛ ጋር

ተያይዞ ይገኛል በማለት አመለከተ።ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሮ የሚከተለው የቅጣት ውሳኔ ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ሊያሳካ እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ 1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትህዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባሉበት በ 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 665(1) ደረጃ የወጣለት ወንጀል በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና አባሪ 3 መሰረት የተመለከተው ደረጃ 3 ሲሆን ተጓዳኝ መነሻ እርከኑም 6 ነው። ስለሆነም የዚህ እርከን መነሻ ፈቃደ ስልጣን/range/ ከስምንት ወር እስከ አንድ ዓመት ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህም መሰረት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ቅጣት ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84 ወይም 85 መሰረት የቅጣት ማክበጃ ያላቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ የመነሻውን ቅጣት እርከኑን ከፍ ሳያደርግ እንዳለ እርከን 2 ን ወስዶታል።

ተከሳሽ በበኩላቸው የቅጣት ማቅለያ አስተያየት ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82(1) ላይ በተመለከተው መሰረት ያላቀረቡ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ከላይ የተገለፀውን እርከን ዝቅ አላደረገውም።

በመሆኑም እርከን 6 ተብሎ ከላይ የተመለከተው የቅጣት ማክበጃ ወይም ማቅለያ ያልቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ በዚሁ ፍቅድ ስልጣኑ መሰረት ተከሳሽ በዘጠኝ ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽ ከአሁን በፊት በሌላ የወንጀል ድርጊት ስማትታወቅ፤ ከግል ተበዳይ ጋር ታርቃ በሰላም እየኖረች መሆኑንና በአሁኑ ወቅት ያለአባት አንድ የ 10 ዓመት ልጅ የምታስተዳድርና የምታሳድግ በመሆኑና ለሕፃኑ ጥቅም ሲባል የእናቱ ከአጠገቡ መኖር አስፈላጊ ስለሆነና በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 36(2) ላይም የተደነገገ ስለሆነ የእስራት ቅጣቱ ከሚፈፀም ይልቅ ለተከሳሽ አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷት ፀባይና አመሏን ማየቱ በቂ ነው ብሎ ፍ/ቤቱ ስላመነ የእስራት ቅጣቱን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 192 መሰረት በሁለት ዓመት ገደብ አግዶታል።

2 ኛ. ተከሳሽ ለመልካም ፀባይ አመራር ዋስትና ይሆናት ዘንድ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 197(2) መሰረት ለብር 500.00(አምስት መቶ ብር) የሚበቃ ዋስትና እንድትጠራ ታዟል። በዚሁም መሰረት ተከሳሽ ቀደም ሲል ለዋስትና ያስያዘችው ገንዘብ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ታግዶ እንዲቆይ ታዟል።

ተከሳሽ ለፅህፈት ወጪ ብር 25.00(ሃያ አምስት ብር) ስትከፍል ትለቀቅ።

3 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

4 ኛ. በዚህ መዝገብ የተሰጠ የዋስትና ግዴታ ካለ ቀሪ ሆኗል።

5 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።